# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

# SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

| | | |
|---|---|---|
| 1ki Diro Kiiro 12<br><br>Hawaasa, Wocawaaro 30, 2013 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundanni Fulinoho<br><br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲፪<br><br>ሀዋሳ መስከረም ፴ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም |



**Amado**

**Lallawu Kiiro 12/2013**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Amaale Mini Borro Mine Uurrisate, Biillonyenna Loou Qeecha Murate Fulino Lallawa …… Qoola ……**

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፲፪/፳፻፲፫**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ …… ገጽ ….**


## LALLAWU KIIRO 12/2013

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Amaale Mini Borro Mine Uurrisate, Biillonyenna Loou Qeecha Murate Fulino Lallawa**

Qoqqowu Amaale Mini addi addi gashshootunna uurrinshate deerri xaadooshshu loossa loosanno borrote mine qoqqowu bayriidi seeri quwa 49 aana xawinsonni kaiminni uurrisa, biilloonyesinna loosu qeechasi seerunni mura hasiissanohuranna;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Bayriidi Seeri quwa 48 cinaancho quwa 3 fidale (a) garinni aane nooha lallamboonni.

## አዋጅ ቁ ፲፪/፳፻፲፫

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ**

የክልሉ ምክር ቤትን ልዩ ልዩ አስተዳደራዊና ተቋማዊ የግንኙነት ሥራዎችን የሚሰራ ጽህፈት ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፱ ላይ በተገለጸው አግባብ ማቋቋም፣ ሥልጣኑንና ተግባሩን በሕግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ ፫ ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**1. Harancho Su'ma**

Konne lallawa **"Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Amaale Mini Borro Mine Uurrisate, Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Lallawa kiiro 12/2013"** yine xawisa dandiinanni.

**2. Tiro**

Qaalu horo wole tiro aanno gede assa hooguro konni lallawi giddo:

1. **"Amaalete Mine"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Amaale Mineeti.
2. **"Songaaficha"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Amaale Mini songaafichaati.
3. **"Koomite"** yaa Amaalete Mini uurrinshunna yannate geeshshi komiteeti.

**3. Koo-teemmate Xawishsha**

Konni lallawi giddo mitte koo-teemmanni xawinsoonni hedo wole koo-teemmano hanqaffanno.

**4. Jeefishshu Mami-Geeshsha**

1. Kuni lallawira worroonniri hasiishshu garinni woraddatenna olluu amaale minna borro minnarano jeefishshu noosiha ikkanno.
2. Konni quwi cinaanchu quwi 1 aana xawinsoonniri noo gedeenni hee'reenna woraddatenna olluu amaale minna borro minna albillitte umonsa dandiite mannu wolqanninna wole jironni ikkado ikkitanno geeshsha taqinsara nooha gashshootu borro mine gutimmate horonsidhanno.

**1. አጭር ርዕስ**

ይህንን አዋጅ **"የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፪/፳፻፲፫"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. **"ክልል ምክር ቤት"** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ነው፤
2. **"አፈ-ጉባኤ"** ማለት የክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ነው፤
3. **"ኮሚቴ"** ማለት የክልሉ ምክር ቤት ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴ ነው፡፡

**3. ስለ ፆታ አገላለጽ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ በአንድ ፆታ የተገለጸው ሀሳብ ሌላኛውንም ፆታ ያካትታል፡፡

**4. የተፈፃሚነት ወሰን**

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ለወረዳና ቀበሌ ምክር ቤት ጽህፈት ቤቶች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች ወደ ፊት ራሳቸውን ችለው በበቂ የሰው ሀይልና ቁሣቁስ እስኪደራጁ ድረስ በአስተዳደር እርከኑ የሚገኘውን የአስተዳደር ጽ/ቤት በጋራ ይገለገላሉ፡፡

**5. Uurra**

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Amaalete Mini Borro Mine konni gedensanni “Borrote Mine” yinanni seeru mannima noosi biso ikke konni lallawinni uurrino.

**6. Borrote Mini Tantano**

1. Borrote mini:

   a) Sooreessa;
   b) Songaafichu amaalaano nna
   c) Woloota songaafichu hunda galtanno biiltonna kaa’lo uytanno loosaasine amadinnoho.

2. Borrote Mini Sooreessi, Songaafichu Amaalaanonna songaafichu hunda galtanno biilto Songaafichunni mootonsantanno.

**7. Borrote Mini Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Borrote minira konni woroonni xawinsoonni biilloonyinna loosu qeechi hee’rannosi;

1. Amaalete Minira borrote owaante aanno;
2. Amaalete Miniranna koomittate gambooshshu hara injjeessanno, qineessanno hattono hasiisanno udiinicho shiqishanno;
3. Amaalete Mini songaale, gumulonna babbaxxitino tajubba garunni borreessantannonna agarantanno gede assanno;
4. Amaalete Minira maxaaffate mini,

**5. ስለ መቋቋም**

የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ከዚህ በኋላ “ጽህፈት ቤት” ተብሎ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**6. የጽህፈት ቤቱ አደረጃጀት**

1. ጽ/ቤቱ፡-

   ሀ) የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ፤
   ለ) የአፈ-ጉባኤ አማካሪዎች እና
   ሐ) ሌሎች ለአፈ-ጉባኤዉ ተጠሪ የሆኑ ተሿሚዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

2. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ፣ ለአፈ-ጉባኤው ተጠሪ የሆኑ ተሿሚዎች እና የአፈ-ጉባኤ አማካሪዎች በአፈ-ጉባኤው ይሾማሉ፡፡

**7. የጽህፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ለምክር ቤቱ የጽህፈት አገልግሎት ይሠጣል፤
2. ለምክር ቤቱና ለኮሚቴዎች የስብሰባ አዳራሽ ያሰናዳል፣ ያደረጃል እንዲሁም የመገልገያ ቁሣቁሶችን ያሟላል፤
3. የምክር ቤቱ ቃለ-ጉባኤ፣ ውሣኔዎችንና ሰነዶችን በሚገባ ተመዝግበው እንዲያዙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

xiinxallotenna mashalaqqete owaante aanno;

5. Amaalete Mini yanna yannatenni fushshanno seera Affini Gaazeexira attamantanno gedenna hajo la'annonsa bissara yannate iillitanno gede assanno;

6. Amaalete Mini widoonni fushshinannire babbaxxitinno borronna maxaafichuwa qixxaawo, attamooshshenna iillishate looso aliidimmatenni massaganno;

7. Songaafichu massago garinni Amaalete Mini miillaranna wosinaho koyishshu owaante aanno;

8. Qoqqowu amaale minenna deerru deerrunkuni noo Amaale Minna dhuka kaajjishate hayyo qineessanno;

9. Amaalete Mini saysanno gumulo hajo la'annonsa bissara yannatenni iillitannonsa gede assanno;

10. Hasaawu umo assine Amaalete mini songora shiqinshoonni hajubba miillate ajayi ajeenna 48 saate giddo iillannonsa gede assanno;

11. Jajju anna ikkate, sheemaate eate qaxxaratenna qaxxaramate dandoo noosi;

12. Seeru garinni woloota loossano loosanno.

**8. Borrote Mini Sooreessi Biilloonyenna Loosu**

4. ለምክር ቤቱ የቤተ መጽሐፍት፣ የምርምርና የመረጃ አገልግሎት ይሠጣል።

5. ምክር ቤቱ በየጊዜው የሚያወጣቸውን ሕጎች በአፍኒ ጋዜጣ እንዲታተሙና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲሠራጩ ያደርጋል።

6. በምክር ቤቱ የሚወጡ መጽሔቶችና በራሪ ጽሁፎች ዝግጅት፣ ህትመትና ሥርጭት ሥራዎችን በበላይነት ይመራል።

7. ከአፈ-ጉባኤው በሚሠጠው አመራር መሠረት ለምክር ቤቱ አባላትና እንግዶች የመስተንግዶ አገልግሎት ይሠጣል።

8. የክልሉን ምክር ቤት ጨምሮ በየደረጃው ያሉ ምክር ቤቶች አቅም የሚጎለብትበትን ስልት ይቀይሳል።

9. ምክር ቤቱ ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንደደርስ ያደርጋል።

፲ ለምክር ቤቱ ጉባኤ የሚቀርቡ አጀንዳዎችን ለአባላት ቢያንስ ከ፵፰ ሰዓት በፊት እንዲደርስ ያደርጋል።

፲፩ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ ይከሣል፣ ይከሳሳል።

፲፪ በህግ መሠረት ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

**Qeecha**

Borrote mini sooreessi aantete xawinsoonni biilloonyina loosu qeechi hee'ranosi;

1. Konni lallawi quwa 7 hunda worroonniha borrote mini biilloonyenna loosu qeechcha jeefisanno;
2. Songaafichu massago garinni borrote mini looso alliidimmatenni massaganno; qineessanno; iillaallisanno;
3. Borrote mini loosaasine sivil serviisete seeri garinni loosoho gaamanno; gashshanno;
4. Borrote minita diru loosu mixonna baajete qixxeesse songaafichaho shiqishanno, fajjinanni woyteno loosu aana hosiisanno;
5. Borrote mini womaashsha faynaansete seeri garinni loosu aana hosiisanno; gashshanno; qorqorshano assiisanno;
6. Borrote mine riqiwe wole sayikki wogane ledo loosu xaadooshshe assanno;
7. Borrote minita loosu rippoorte songaafichaho shiqishanno;
8. Songaafichunni uynanisiha wole loosu qeecha loosanno.

**9. Baajete**

Borrote mini baajete Amaalete Mini gaamanno.

**10. Shallaggote Tajubba**

**8. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር**

የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ስር የተመለከቱትን የጽህፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
2. አፈ-ጉባኤው በሚሠጠው አመራር መሠረት የጽህፈት ቤቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤
3. የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
4. የጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለአፈ-ጉባኤ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
5. የጽህፈት ቤቱን ሒሣብ በፋይናንስ ህግ መሠረት ያንቀሳቅሳል፣ ያስተዳድራል፣ ያስመረምራል፤
6. ጽህፈት ቤቱን ወክሎ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤
7. የጽህፈት ቤቱን የሥራ ሪፖርት ለአፈ-ጉባኤው ያቀርባል፤
8. በአፈ-ጉባኤው የሚሠጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

**9. በጀት**

የጽህፈት ቤቱ በጀት በክልሉ ምክር ቤት ይመደባል።

Borrote mini wo'manna halaalaancho shallagote tajubba amadanno.

**11. Wodho Fushsha Lainohunni**

Amaalete Mini konne lallawa jeefisate hasiissanno wodho fushshara dandaanno.

**12. Loosu Aana Hossannokki Seerubba**

Konne lallawi ledo kiphi yaano aye seerinna rosamino asooti konni lallawinni hanqafantino hajo lainohunni jeefishshu dinonsa.

**13. Lallawu Kaajjanno Yanna**

Kuni lallawi Wocawaaro 30/2013 M.D hanafe kaajjinoha ikkanno.

**Hawaasa, Wocawaaro 30, 2013 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

**፲ የሒሳብ መዛግብት**

ጽህፈት ቤቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

**፲፩ ደንብ ስለማውጣት**

ምክር ቤቱ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፪ ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ሕጎች**

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ ለተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡

**፲፫ አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከመስከረም ፴ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ሀዋሳ፣ መስከረም ፴ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም**

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳደር**